# በጎመን ጥላ ተጠልሎ ይታያል ዝሆን ተንጋሎ

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

<u>መንደርደሪያ :</u>

1. « አህያ ምን ትጫናለች እንጂ ምን ትበላለች ተብላ አትጠየቅም »

የምርጫ ስነምግባር ተፈራራሚ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸሙት ደባ ::

እኛ ገጣባ አህዮቹ ኢትዮጵያውያንን ዱቄት፤ ጨው፤ በርበሬ፤ ቢያሻቸው አመድ፤ እንዴት በገጣባው ወገባችን ላይ እንደሚጭኑብን ያደረጉት የጋራ ስምምነት ::

2. « ዕብድ ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው »

ለአቶ መለሰ ዜናዊ፤

ስልጣን አለቃለሁ ባሉን ማግስት ፋርሽ ባትሉኝ እንደገና ! በማለታቸው ::

3. « ተናግረን ነበረ ባጥር ተንጠልጥለን፤

ወያኔ ሽፍጥ እንጂ ሃቅ አያውቅም ብለን »

ለኢ/ር ኃይሉ ሻውል

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰብአዊ መብት በመግፈፍ:የሕዝባችንን የማሰብ ነፃነት ገድቦ፤ የመፃፍ: የመናገርና: የመሰብሰብ መብቶቹን በከለከለበት፤ ሕዝባችንን በዘርና በጎሳ መሃረብ ዐይኑን ጋርዶ እያደናበረ ባለበት፤ ሠራተኛው የሥራ ዋስትናውን ባጣበት፤ ገበሬው ከእርስቱ ተነቅሎ ለባዕዳን የአገራችን መሬት እየተቸበቸበ ለእጅ አዙር ቅኝ ተገዥነት እያመቻቹን ባለበት፤ ትልቅ አገር የወረሱ ትንንሽ ፍጡራን አገራችን ኢትዮጵያን በየማዕዘኑ ሸራርፈው እያሳነሷትና እየበታተኗት በዚህ ድርጊታቸው ሕዝብ አክ ብሎ ተፍቷቸው ለመውደቅ እየተንገዳገዱ ባሉበት ወቅት የወያኔ የሸንበቆ ከዘራ በመሆናቸው ::

4. « ያንዱ ጉዳይ ለሌላው የእንጀራ ልጁ ነው »

በረሃብ የሚያልቀው የኢትዮጵያ ሕዝብና ወያኔ

5. « አሳቀኝ ገንፎ ከምሳዬ ተርፎ »

ለአቶ ልደቱ አያሌው

ለዳግም ክደት፤ ከልደታ ወደ ላሊበላ ላደረጉት ስደት ::

አልሰማም አንልም ሳሰታ ሳሊበል፤

ባንድ ቢላ ሳይሆን በሁለት ሲበላ፤

ሸዋን ሳፍ አድርጎ ለምሳ ለቁርሱ፤

ሳሊበላ ገባ ሊያርደው በደንደሱ ::

6. « ወገኛ ገንፎ አድሮ ይፋጃል »

ለዶ/ር አሸብር ወልደ ጊዮርጊስ (የቀድሞ እግር ኳስ ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት)

« የኔ ኢላማ ኢህአዴግ አይደለም ኢህአዴግን የምቃወም አይደለሁም ለመልካም አስተዳደር እጦት ....እንቅፋት የሆነውን ግለሰብ በሕዝብ ካርድ እንዲወጣ ማድረግ ነው »

7. « ከጅብ ቆዳ የተሰራ ክራር ቅኝቱ እንብላው ! እንብላው ! ነው »

ለሻዕቢያ

8. ቃል ዕምነት፤ ዕምነት ድርጊትን፤ ድርጊትም ተስፋን፤ ወልዶ ለድል ያበቃል ::

ለ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደግሳ

9. « አያያዙን አይተህ ጭብጠውን ቀማው »

ለኢትዮጵያ ሕዝብ

10. « ሰዶ ማሳደድ ካማረሽ ዶሮሽን በቆቅ ለውጪ »

ለአንድነቶች

# መግቢያ

## «እንዲህ ያለ ዘመን የዘመን ስልቻ፤

## ወታደር በቢሮ ምሁር በዘመቻ»

ብሎ አዚሞ ነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ ደርግ (ወታደራዊው መንግሥት) የዩኒቨርስቲ መምህራን፤ ተማሪዎችንና የአስተዳደር ሠራተኞችን፡ ለሰፋሪዎች የጎጆ ሥራ ወደ መተከልና አሶሳ ባዘመተበት ዘመን።

እኔ በነበርኩበት የጉምላክ ዘመቻ ጣቢያና በፓዌ፡ ስለነበረው ሁኔታ ሌላ ጊዜ በሌላ ርዕስ እመለስበታለሁ፡ ለጊዜው የተነሳሁበት ጉዳይ ሰላልሆነ።

ታዲያ ዛሬም በያዝነው «ዘመነ ስልቻ»

እናቶች ለሃዘን፤ አባቶች ለትካዜ፤ ወጣቶች ለስደት፡ ለእስርና ለሞት፤ ሕፃናት ለረሃብና ለበሽታ፤ ምሁራን ለስደትና ለውርደት፤ ገበሬው ከርስቱ ለመነቀል፤ ሠራተኛው ከሥራው ለመባረር፤ ጋዜጠኛው ለእስርና ለስደት፤ እንዳው በጥቅሉ፡

አገር ለድቀት፤ ታሪክ ለክደት፤ ቋንቋ ለመከፋፈያ፤ ባሕል ለብረዛ፤ ሃብት ለምዝበራ፤ ስልጣን ለንቅዘት (ለሙስና) ለሆድ መሙያ፤ በራስ መተማመን ትምክተኛ ተብሎ ለመሰደቢያ፤ መማር ሃጥያት፤ መጠየቅ ወንጀል፤ ማሰብ ክልክል፤ መጻፍ የሚያስከስስና የሚያሳስር ብሎም የሚያስገድል፤

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ የተጠላበት፤ የተናቀበት፤ የተዋረደበት፤ የተራበበት፤ በአንፃሩ የአገሩ ሃብት ወርቁ፤ አልማዙ፤ ቡናው፤ ፤ ሌጠው፤ ዕሕሉ፤ መሬቱ፤ የተወደደበትና የሚመዘበርበት፤ ለማንም ባዕድ በርካሽ የሚቸበችብበት፤ ዘመን ላይ ደርሰናል።

«የዘመን ስልቻ ከስልቻም ስልቻ» ይሏችኋል ይህ ነው።

የ2002 ዓ.ም. ምርጫ በጠራራ ፀሐይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንጅራት በሚመቱ፡ የፖለቲካ ቁማርተኞች መሃከል፡ ሃቅን ውጦ፤ ወገን ክዶ፤ ሆድ ለመሙላት፤ ደንደስን ለማደለብ፤ አንድ አለኝ፤ ሁለት አለኝ፤ እያሉ አኪር በሚሰበስቡ፡ ሕሊና ቢሶች መሃከል የሚካሄድ እንጂ፡ ሃቀኛ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበት አይደለም።

የትናንት የትግል ጓዶቻቸውን ለወያኔ በእጅ መንሻነት አቅርበው ዘወር ላሉ ቁማርተኞች ለነገው የፖለቲካ ክስረታቸው ማን ዳግም ለነሱ የመሰዋዕት ጠቦት ለመሆን ከነሱ ጎን ይቆማል? ፖለቲካ የዕምነትና የድርጊት ውጤት መሆኑ ቀርቶ፡ የእንጀራ መብያቸው ላደረጉ ሞያ ቢሶች ከፖለቲካው ጎራ ከተወገዱ ሠርተው የሚበሉበት ሞያ ስለሌላቸው፡

ፖለቲካን ሙጥኝ በማለት፡ እንደ አልቅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ጉሮሮ ላይ ተጣብቀው፡ ደሙን በመምጠጥ መደለብን ይመርጣሉ።

ወገን ለችግር፤ ለረሃብ፤ ለጥቃት፤ ለስደት፤ ለሁለተኛ ዜግነት ብሎም ለባርነት ሲዳረግ ከተበደለው ወገናቸው ጎን በመሆን ለፍትህ፤ ለእኩልነት፤ ለሕግ የበላይነት መቆም አይሆንላቸውም። ከንግዲህ ወዲያ በየ ድልድዩ ስር ተሸሽጎ ማንጅራት ለመምታት አመቺ ጊዜ የሚጠብቅ የፖለቲካ ቁማርተኛ ሁሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ቁማር መቆመሩን ማቆም ይኖርበታል።

እስቲ ጥቂት ጥያቄዎችን እናንሳ፤

- ሰነምግባር ምንድነው?
- የሰነ ምግባር ሰምምነት ለምን አሰፈለገ?
- ማንሰ ባለጌ? ማንሰ ጨዋ ሰለሆነ ?

ሰነ ምግባር ማለት በነሱ መሰፈርት ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በቀር የአንድ ነገር ወይም ጉዳይ በወጉ፤ በደንቡ፤ በሕጉ መሠረት መፈጸም ወይም መደረግ ማለት ሲሆን፡ በዚህ ይዘት ምርጫው በሕገ መንግሥቱ መሰረት መፈጸም ያለበት መሆኑን ያመለክታል።
በአንድ አገር ማንኛውም ዜጋ ሊያከበርው የሚገባ ሕገ መንግሰት ካለ፤ ከሕገ መንግሥቱ በላይና በታች የሆኑ የተለያዩ ዜጎች ከሌሉ፤ ሕገ መንግሥቱ አንዱን እየሳመ ሌላውን ካልነከሰ፤ አንዱን እያቀፈ ሌላውን ካልገፈተረ፤ አንዱን አጥግቦ ሌላውን ካላሰራበ፤ አንዱን ሰብስቦ ሌላውን ካልበተነ፤ አንዱን አስተምሮ ሌላውን ለመሃይምነት ካልዳረገ.....ወዘተ በስተቀር ዜጎች ሁሉ ለሕጉ ተገዢ ሰለሚሆኑ ከሕገ መንግሥቱ በላይ ሌላ ሕግ የሚያስፈልግበት ምክንያት አይኖርም።
ወያኔ እራሱ ያወጣውን ሕገ መንግሥት እራሱ እንደማያከብር፡ የጦር ሃይል፤ የፖሊስ ሠራዊት፤ የመገናኛ ብዙሃን፤ የምርጫ ቦርድ፤ የአገሪቱን ሃብትና ፍርድ ቤቶችን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ፡ እስርና የሞት ፍርድ እንደ ልመና ሰንዴ እያከፋፈለ ባለበት ወቅት፡ የምርጫ ሰነምግባር ብሎ ማላዘን « የዘፈን ዳድዳሩ እስክስታ » እንዲሉ ነው።
ይልቁኑ ለነማን እየተደገሰ ነው? ማንን ታማኝ ተለጣፊ ለማድረግ? ማንን ለማስፈራራት? ማንን ለማሰር? ማንን ለመግደል? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን።

*በ 97ቱ ምርጫ ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ የተሰላ አደጋ፡ በሳቸው ቋንቋ* (Calculated risk) *ወሰደን ነበር፡ አሁን ያንን እንደግምም እያሉን ነው።*

*አቶ መለስ ዜናዊ አለመታደል ሆኖ፡ የሂሳብ ትምህርትና ኢትዮጵያዊነት አለርጂክ ሆኖ ሰውነታቸውን እያሳከከ ያስቸግራቸዋል፡ በመሆኑም በሳቸው ስሌት አንድና አንድ ሁሌም አንድ እንጂ፡ ሁለት የሆነበት ጊዜ የለም።*

*በወጉ ከተሰላ አንድና አንድ ይሆናል ሁለት ሲሆን፤ ካተረፈም ከዛ በላይ ሦስትም አራትም ይሆናል፤ ካከሰረም ከአንድ በታች ዜሮም፤ ከዜሮም በታች ወርዶ ብድር ሊያስገባ እንደሚችል የጨዋ ጠራጊ (ሊስትሮ) ወንድሞቻችን እንኳን ጠንቅቀው ያውቁታል።*

*በተጨማሪ « ያለው አማራጭ አንድና አንድ አንድ ነው ይላሉ » ይህ ያቶ መለስ አንባ ገነናዊ ገጸ ባህሪይ ሲሆን፡ ይህም እኔ ካልኩት ውጭ የሌሎችን ሃሳብ አልቀበልም፡ ሌላም አማራጭ የለም የሚለው እስታሊናዊ ጸባያቸው ነው።*

*ሌላው « ችግርን መቅረፍ » ያዘወትራሉ።*

*ችግርን ለአንዴና ለመጨረሻ ከማስወገድ ይልቅ፡ ችግርን እንዳይደርቅ በየጊዜው እየቀረፉ እንደገና እንዲቆሰልና እንዲያመረቅዝ በማድረግ፡ ለልመና አቁምዳ መሙያ በዓለም ዙሪያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብርና ሰብዕና ለማቁሰያ ይጠቀሙበታል።*

*በጥቅሉ ወያኔ ዘወትር አፍርሶ መግንባት እንጂ፡ በነበረው ላይ መገንባት የማይሆንለት፡ ዘወትር ጀማሪ፤ በእቅድ ሳይሆን በደመነብስ፤ በሂደት ይታያል እያለ በጭፍን የሚደናበሩ የዘረኞች ቡድን ሲሆን፡ ምኞቱ በአንዲት ኢትዮጵያ ጥላ ስር ተሰባስቦ ለጋራ ጥቅምና እድገት መቆም ሳይሆን፡ ከደደቢት በረሃ ይዞት በመጣው አጀንዳ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተዘረፈ ሃብትና ንብረት፡ የትግራይ ሪፐብሊክን የመመስረት ሕልሙን ዘወትር የሚቃዥ ቡድን ነው ።*

*በመሆኑም ለትግራይ ሕዝብ « ከወርቅ የተገኘሁ » የሚል የአፍ ጨዋ በማስቀረፕ፡ የትግራይን ሕዝብ ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኑ በመነጠል፡ ለእኩይ ተግባሩ በከዘራነት ይጠቀምበታል። በዚህ አጋጣሚ ወገናችን ለሆነው የትግራይ ሕዝብ የምናስተላልፈው ጥሪ ቢኖር፡ የወያኔን እኩይ ተግባር ተገንዝቦ፡ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሆን አገሩን መታደግ፡ ወይም ወያኔ በሱ ስም እየጠበሰ እንዲሸተው ብቻ እንጂ የማያቀምሰውን ጨዋ እየቋመጠ « ወጉስ ማዕረጉስ » እያለ መቀጠል ይሆናል።*

- *ለመሆኑ የክህደት ምክንያቱ ምንደነው ?*
- *መቼስ ተጀመረ ?*
- *ማንስ ጀመረው ?*
- *ማን ማንን ካደ ?*
- *በክህደትስ ምን ትርፍ ተገኘ ?*

*ለነዚህ ጥያቄዎች ፡ ከአገራችን ሁኔታ አኳያ መልስ ለማግኘት እስቲ አብረን እንዳስ ::*

*ለክህደት በዋናነት እንደምክንያት የሚጠቀሰው የስልጣን ጥም ሲሆን፤ በመከተልም ታዋቂ (ዝነኛ) የመሆን ፍላጎት፤ ለሆድ ማደርና የአልጠግብ ባይነት ፡ ተደማምረው የሰውየውን አይምሮ ይደፍኑታል ፡ ዐይኑን ይጋርዱታል፤ ጆሮውን ይደፍኑታል :: እምነት በጣሉበት ሰዎች ላይ ፡ ውሸትና ክህደት ያዘወትራል ፡ ከዚህም የተነሳ አብረውት በሚሰሩ ሰዋች ላይ ፡ ለራሱ አላማ መሳካት ሲል ማንኛውንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይመለስም::*

*የሚገርመው ክህደት በሰው ልጅና በእግዚአብሄር መሃከል ተጀመረ የሚሉ ፡ በአቤልና በቃኤል መሃከል ለተፈጠረው ችግር ፡ እግዚአብሄር ቃኤልን « ወንድምህ አቤል የት አለ ? ብሎ ቢጠይቀው እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን ? » ብሎ መልስ በመስጠት ጀመረ የሚሉ ሲኖሩ :: በሌላ ወገን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ85 ዓ.ዓለም በተወለደው በማርቆስ ጀኑስ ብሩቱስ ካፒኦ እና ፡ በቄሳር መሃከል ተጀመረ የሚሉ የታሪክ ጠበብት አሉ ::*

*ማን ማንን ካደ ? ለሚለው በቀላሉ ከክርስቶስና ከይሁዳ በኋላ ያለውን እንኳ ብንቃኝ ብዙ መጥቀስ ይቻላል ፡ በበኩሌ በመንደርደሪያዬ ላይ ጨረፍ አርጌ ስላለፍኩ በጎደለ እናንተ ሙሉበት ::*

*ያም ሆነ ይህ ፡ ለኛ የድርጊቱ አስከፊነትና ውጤቱ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት በቀላሉ እንዳናየው ያስገድደናል ::*

*በክህደት ምን ተገኘ ለሚለው ?*

*በሕዝብ መተፋት፤ ቅሌት፤ ከራስ ተርፎ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ ተወቃሽነት፤ እንደራስ ጥላ ዘወትር እየተከተለ የሚያሳድድ የደም ጩኸት፤ በመጨረሻም ቀባሪ ያጣ ሞት መሞት ናቸው :: ከዚህ ፈጣሪ ይሰውረን !!*

ታዲይ ቅንጅት ከ97 ምርጫ መጭበርበር ጋር ተያይዞ ላቀረባቸው 8 ነጥቦች አንዱም እንኳን መልስ ባላገኘበት ወቅትና ሁኔታ ከወያኔ ጉያ ሄዶ መወሸቁ ለምን አስፈለገ?

በአሁኑ ወቅት ከኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ይልቅ፡ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደግሳ ነፃ ሰው ናት፡ ምንም እንኳን የወሕኒ ቤት ኑሮ ባይደላም፡ የሀሊና ወቀሳ እንደ አባጨንጓሬ እየኮሰኮሰ እንቅልፍ አይነሳትም::
እንጂነር ኃይሉ ሻውል ግን የነበራቸውን ነፃነት፡ የምርጫ ስነምግባር ውል ከወያኔ ጋር በመፈራረም እጅና እግራቸውን ታስረዋል:: በዚህም ለወያኔ የዘረኝነት አገዛዝ ዕድሜ ቀጥል በመሆን ምናልባት በመቶ አለቃ ግርማ ምትክ የቤተ መንግስት ጠባቂነት ከወያኔ በርጥባን መልክ ይችራቸው ይሆናል::
በጎመን ጥላ ተጠልሎ ይታያል ዝሆን ተንጋሎ ይሏችኋል ይህ ነው::
በዚህ ድርጊታቸው የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አጽም ይንቀጫቀጫል፤ ደማቸው እንደ አቤል ደም ጩኸቷን ታሰማለች፤ ሥጋቸው ሰላም ስለተነፈገው በኢትዮጵያ የመሬት መናወጥ ይሆናል::

<u>መዝጊያ</u>

«አብረን ዝም እንበል»

ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድን

«....በአፎይታ ጥላ እንጠለል፤

ዝም ብለን አብረን ዝም እንበል፤

......በቆይታ፤ በጸጥታ፤ ዝም ብለን አብረን .....ዝም እንበል::

ሳንናገር፤ ሳንጋገር፤

.....ሞራችንን ሳናሰነብብ ሳንቀባጥር፤

ዳግመኛ ሞት እንዳንሞት፤

አዲሰ ቀን እንዳይጨልም

....እንበል አብረን ዝምምምምምም»

*በ2002 ዓ.ም. ሊደረግ የታሰበው ምርጫ ሕዝብን የማይወክል የፖለቲካ ሽፍጠኞች ተራ ማስመሰያ በመሆኑ በሕዝባዊ እምቢተኝነት፤ በሕዝባዊ አመጽ መገታት ይኖርበታል ።*

*ወፍራም ቆዳ አብቅለን በደልን ለመሸከም ካልተላመድን በቀር ፡ አያቶቻችንና አባቶቻችን ፡ ጣሊያንን እንደበርበሬ የለበለቡት ፡ በየ ጎበዝ አለቃው በመሆን እራሳቸውን በማደራጀት ባገራቸው በወንዛቸው ፡*

*« ሰው ባገሩ ፡ ሰው በወንዙ ፡ ቢበላ ሳር ቢበላ መቅመቆ፤*

*ይከበር የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ » ብለው ባደረጉት ትግል ስለሆነ፤*

*ዛሬም ሌላ ዘርአይ ደረስ፤ ሌላ በላይ ዘለቀ፤ ሌላ አብዲሳ አጋ፤ ሌላ አሉላ አባ ነጋ፤ ሌላ ኡመር ሰመተር፤ ሌላ ኃይለማርያም ማሞ፤ ሌላ ገረሱ ዱኪ.....ወዘተ ከመሃከላችን በመፍጠር ለአገራችንና ለሰንደቃችን ዘብ በመቆም ከትውልድ ተወቃሽነት በመዳን ለተተኪው ትልድ እኛም ነፃ አገር ማስረከብ ይኖርብናል ።*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !*

*እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይባርክ !!*

*የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. (February 22/2010)*